# እስትንፋስህ ተገታ፡

ስሙ ሞት የሚባል የማይቀር እንግዳ ፣
ሌሊት ከተፍ አለ በጥላሁን ጓዳ።
ምንኛ ክፉ ነው ሞት የሚሉት አውሬ ፣
ታግሎ ይዞት ሄደ ጥላሁንን ዛሬ።
ኧረ በሕግ አምላክ ሕግ ያግድህ ስማ ፣
ወገን በተኛበት ደርሰህ በጨለማ ፣
እንዴት ሀብታችንን ጨክነህ ወሰድከው ፣
የኢትዮጵያን ብርሃን ይኼንን ታላቅ ሰው።
ደፋር አይደለህም ሞት ለካስ ፈሪ ነህ ፣
ወገን በተኛበት ሌሊት ትመጣለህ።

ጥላሁን ገሠሠ የወገን አለኝታ ፣
ክቡር እስትንፋስህ በዚች ቀን ተገታ።
አገሬን እያለ የሚጮኸው ድምፅህ ፣
ኢትዮጵያን የሚለው ብርቅዬ አንደበትህ ፣
ዳግም ላይናገር አሸለበ ለአንዴ ፣
ተጠየቅ ጥላሁን እንዲህም አለ እንዴ?

አካል የሚያስቆርጥ ሕመም ያልደፈረህ ፣
ከአንገትህ ያረፈው ስለት ያልገደለህ ፣
እንዴት ሳትታመም አውርተህ ተጫውተህ ፣
በሌሊት የመጣ ክፉ ዕንግዳ ያዘህ?

ይገርማል ጥላሁን በሰላም አምሽተህ ፣
ሌባው ድንገት መጥቶ በሌሊት ወሰደህ።
በምድር እንዳትታይ ለአንዴም ለዘላለም ፣
አትሞብህ ሄደ የሞትን ማኅተም።

ለምትወደው ሕዝብህ እንዲያ ለምታምነው ፣
ምሥጢር የሸሸግከው ዘንድሮ ብቻ ነው።
የወገንን መራብ አልቅሰህ ስትነግረው ፣
የኢትዮጵያን ደስታ በመድረክ ስትገልጸው ፣
ምን ነገር ተገኘ እንዴት ብትጨክን ነው?
እንዲህ ላትመለስ ወጥተህ ቅርት ያልከው።

እጅግ በምትወደው በአገርህ በምድርህ ፣
የእስትንፋስህ ማብቂያ ሆነ ስንብትህ።
«ዋይ! ዋይ!» ሲሉ ብለህ ያለቀስክላቸው ፣
ለእነኛ ረሀብተኞች ዕንባ ለሌላቸው ፣
መንታ መንታ ሲወርድ እንዲያ ሲፈስ ዕንባህ ፣
የታሪክ ቅርስ ሆኗል የመድረክ ላይ ሲቃህ።
ዛሬም ሁሉ አዘነ ሁሉ አለቀሰልህ ፣
«ዋይ! ዋይ!» ይል ጀመረ የምትወደው ሕዝብህ።
አንገትህ በካራ በስለት ተወግቶ ፣
አገሬን ይል ነበር ድምፁን አሰምቶ።

አካልህ ተቆርጦ ለአንተ ማሰብ ትተህ ፣
«ወገን እባካችሁ ስለ ወገን» ብለህ ፣
ታሰባስብ ነበር ገንዘብ ለደሃው ሰው ፣
የሚታከምበት አጥቶ ለቸገረው።
ኢትዮጵያ አትረሳውም ይኸንን ውለታ ፣
መልካም ማድረግህን ሥራህን ለአንዳፍታ።

የቆምክበት መድረክ ለኢትዮጵያ አንድነት ፣
የእናት አገርህን ስም የጠራህበት ፣
ባየኸው ጥላሁን ሰፈር እና አገሩ ፣
የኀዘን ቤት መስሎ ከተማው መንደሩ።

ጥላሁን ገሠሠ ሞትህ ሞት አይደለም ፣
ትውልድ ያነሣዋል ስምህን ዘላለም።
ሰው ሳያስታምምህ ወገን ሳይጠይቅህ ፣
ጥላሁን በመንገድ ድንገት ወጣ ነፍስህ።
ለስንቱ የደረስክ በኀዘን በችግሩ ፣
አቤት! በዚያች ሌሊት ሰው ጠፋ በምድሩ።

እባክህ እግዚአብሔር ይኼንን ታላቅ ሰው ፣
እንደ ቅዱሳኑ ሞቱን ሞት አታርገው።
ተስፋ ላሚጠጥነው ለምንወደው ወገን ፣
ጥላሁን አልሞተም አንቀላፍቷል በለን።
እንደ አልዐዛር ጠርተህ መግነዙን ፍታለት ፣
ሞቱ ሞት እንዳይሆን የጥላሁን በእውነት።

ታማሚን ጠይቋል የታረዘ አልብሷል ፣
ለተራበ አብልቶ እስረኛን ጎብኝቷል ፣
ሙያው ብቻ ሳይሆን የልቡ ደግነት ፣
ዋይ! ብሎ አስጨሆታል ለራብ ለጦርነት።
አባት መልካም ግብሩን ይኼን ቁጠርለት ፣
ልጅህን ክርስቶስ አኑረው በገነት።

ጥላሁን ገሠሠ የወገን አለኝታ ፣
ክቡር እስትንፋስህ በዚች ቀን ተገታ።
አገሬን እያለ የሚጮኸው ድምፅህ ፣
ኢትዮጵያን የሚለው ብርቅዬ አንደበትህ ፣
ዳግም ላይናገር አሸለበ ለአንዴ ፣
ተጠየቅ ጥላሁን እንዲህም አለ እንዴ?

ደህና ሁን ጥላሁን እግዚአብሔር ያስብህ ፣
በገነት ይቀመጥ የከበረ ነፍስህ።

ወ ስ ብ ሐ ት ለ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር!

አብርሃም ሰሎሞን
ሚኒሶታ አሜሪካ
Abraham.solomon@yahoo.com